# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ግንቦት 13 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሰራተኞቹ መገደል ምክንያት በኢትዮጵያ እርዳታ መስጠቱን አቋረጠ፤**

**አድማ አነሳስታችሁዋል የተባሉ የታክሲ ሹፌሮች ታስረው ተደበደቡ፤**

**ቤተክህነት በጳጳሳት ሽኩቻ ስትታመስ ሰነበተች፤**

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ለተራቡት ወገኖች ሲያደርገው የነበረውን የምግብ ድጋፍ አቋርጦ መውጣቱን ሰሞኑን በይፋ ገለፀ::

በምስራቅ ኢትዮጵያ ክልል ውስጥ በርሀብ እየሞቱ ያሉትን ዜጎች ለመታደግ እየተንቀሳቀሱ በነበሩት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ ፕሮግራም ሰራተኞች ላይ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም በተሰነዘረ ጥቃት አንድ ሰው በመገደሉና ሌላው ክፉኛ በመቁሰሉ ድርጅቱ ስራውን አቁሞ ከአካባቢው መውጣቱን ለማወቅ ተችሏል::

እንደ ወትሮው ቀን ሁሉ የሰው ህይወት ለማትረፍ ደፋ ቀና እያሉ በነበሩት የድርጅቱ ሰራተኞች ላይ ድንገት ለግዜው ባልታወቁ ታጣቂዎች በተሰነዘረባቸው ጥቃት የሞት እና የመቁሰል ብሎም የመሰወር እርምጃ የተወሰደባቸው ሲሆን ይህንኑ እርምጃ ተከትሎ ድርጅቱ ስራውን ለማቆም መገደዱን ባወጣው መግለጫ አስታውቆዋል::

በተደጋጋሚ ግዜ ድርቅ በሚያጠቃው በዚሁ ክልል ውስጥ ለህዝቡ የምግብ እርዳታ በማድረስ ላይ በነበሩት ሰራተኞቹ ላይ ረቡዕ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም ረፋዱ ላይ ድንገት የታጠቁ ኃይሎች

በቦታው በመድረስ አሰቃቂ የሆነ እርምጃ ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ ሁለት የድርጅቱን ሰራተኞች አፍነው የወሰዱዋቸውና እስከ ዛሬ ድረስ የት እንደደረሱ ባለመታወቁ ድርጅቱ የጀመረውን የነፍስ አድን ስራ ለማቆም መገደዱን ባወጣው መግለጫ ገልፆዋል::

በሁኔታው የተደናገጡት የተባበሩት መንግስታት የምግብ ድርጅት ከፍተኛ ኃላፊዎች በአካባቢው ያለውን የፀጥታ ሁኔታ በአንክሮ እየተከታተሉ ከመሆኑም በላይ ወንጀሉን የፈጸመውን አካል ለይቶ ለማውጣትም እየሰሩ መሆኑም ተጠቁሞዋል::

ሁሌም ስጋት እና ጭንቀት የማይለየው የምስራቅ ኢትዮጵያ ክልል ከዚህ ቀደም ነዳጅ ቁፋሮ ላይ በተሰማሩ የቻይና ዜጎች ላይ ድንገተኛ እልቂት መፈፀሙ የሚታወስ ሲሆን ዘንድሮም ለሰብአዊ እርዳታ ተግባር በመንቀሳቀስ ላይ በነበሩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰራተኞች ላይ ይህን የመሰለ አሰቃቂ እርምጃ መወሰዱ አሳዛኝ መሆኑ እየተገለፀ ይገኛል::

ጉዳዩን አስመልክቶ የወያኔ ቡድን በአካባቢው ጠፍቶዋል እያለ ሲለፍፍበት በነበረው የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦብነግ) ላይ ጣቱን ቢቀስርም ግንባሩ በበኩሉ ወያኔ ገመናዬ ለምን ተጋለጠ በሚል የወሰደው እርምጃ ነው እያለ መልሶ መወንጀሉም ታውቆዋል::

በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ውስጥ የተከሰተወ ረሀብ ከፍተኛ እልቂት እያደረሰ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔ ቡድን ቅድሚያ ለዜጎች ህይወት መታደግ ሲገባው ትኩረት ሳይሰጥ በመቅረቱ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በቦታው ተገኝቶ የሰብአዊ እርዳታ እየፈፀመ መሆኑ ግልፅ ነው:: የወያኔ ቡድን ምስጥሬ ለምን ተጋለጠ በማለት በዓለም አቀፉ ድርጅት ሰራተኞች ላይ የወሰደው የግፍ እርምጃ ነው በማለት በአከባቢው የሚገኙ ተቃዋሚ ኃይሎች ክስ ሰንዝረዋል::

በኦሮሚያ ቦረና ......በሱማሊያ ኦጋዴን...... በአፋር ሰመራ......በሐረር ብዙ ቦታዎች..... በአማራ ጎጃም ወሎ ......በባሌና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የተከሰተው ርሀብ ከቀን ወደ ቀን እየተስፋፋ መጥቶ ከህፃን እስከ አዛውንት እየፈጀ ባለበት በዚህ ቀውጢ ወቅት ለወያኔ የእድሜ ማራዘሚያ በሆነው የአባይ ግድብ ግንባታ ቅስቀሳ ተሸፍኖ እንዲያልፍ ቢፈለግም የተባበሩት መንግስታት የምግብ ፕሮግራም በቦታው ተገኝቶ ሁኔታውን ይፋ በማድረጉ እና የረሀብተኛውን ቁጥር ጭምር በማጋለጡ የተበሳጩት የወያኔ ባለስልጣናት የራሳቸውን ታጣቂዎች አስርገው አስገብተው ያስወሰዱት እርምጃ ነው ተብሎ እየተናፈሰ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በስፍራው በስፋት ይንቀሳቀስበታል ተበሎ በሚነገርለት በኦብነግ ታጣቂዎች የተወሰደ ድንገተኛ ጥቃት ሳይሆን አይቀርም እየተባለም ይገኛል::

የወያኔ ቡድን ሲጨንቀው ማስተንፈሻ ይሆነኛል በሚል በህዝብ ላይ የሚወስደውን የግፍ እርምጃ መልሶ ተቃዋሚዎችን በአሸባሪነት እየወነጀለ የነበረ ቢሆንም ዛሬ ግን እውነታው ተጋልጦ የአሸባሪነት ስራ እየሰራ ያለው እራሱ ወያኔ መሆኑን ህዝቡ ጠንቅቆ ያወቀበት ግዜ ላይ ደርሶዋል ሲሉ የተቃዋሚ አመራሮች እየገለፁ ይገኛሉ::

የወያኔ ቡድን ከኦብነግ አመራሮች ጋር የእርቅ ስምምነት ተፈራረምን ከእንግዲህ በምስራቅ ኢትዮጵያ አንዲት ጥይት አትጮህም እያለ ሲለፍፍ የነበረ ቢሆንም እውነታው ግን ዛሬም ኦጋዴንን ጨምሮ በምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ የሽምቅ ውጊያ እንዳለና አካባቢው አሁንም የስጋት ቀጣና መሆኑን

የጠቆሙት የክልሉ ነዋሪዎች ወያኔ ለግዜያዊ የፖለቲካ ፍጆታ ሲል ብቻ ከድርጅቱ በስነ ምግባርና በተለያዩ ችግሮች የተባረሩትን ሰዎች ሰብስቦ ስምምነት ተፈራረምኩ ማለቱ የልጆች እቃ እቃ ጨዋታ ነው ሲሉም ይናገራሉ፡፡

ባለፈው ሳምንት እሁድ እለትም በጅቡቲ የሚገኙ የኦብነግ አባሎች ናቸው የተባሉትን ሰብስቦ የበደልነውን ህዝብ እንክሳለን ብለዋል በሚል ባዶ ፕሮፓጋንዳ ቢነዛም የተባሉት ሰዎች ስራ አጥ ሆነው በጅቡቲ ኑሮዋቸውን የመሰረቱ እና በርሀብና በችግር የተሰደዱ ኢትዮጵያውያኖች መሆናቸውን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ይገልፃል፡፡ ብዘዎቹ የክልሉ ነዋሪዎች  በሀገሪቱ ነፃነት በጠፋበት.....የህግ የበላይነት ጨርሶ በተደመሰሰበት.....የፖለቲካ ነፃነት ደብዛው በጠፋበት.......ግልፅነት እና ተጠያቂነት ገደል በገባበት......ቡድንተኛነት በሀገሪቱ በነገሰበት በዚህ ግዜ በሀገሪቱ ውስጥ የተረጋጋ ሰላም አለ ወደ ሀገራችሁ ግቡ እየተባለ ቅስቀሳ መደረጉ የሚያሳዝን ጭፍን ያለ ውሸት ነው ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ይናገራሉ፡፡

ባለፈው ዓመት የወያኔ ቡድን ከኦብነግ አመራሮች ጋር ስምምነት አድርገናል በሚል በተለያዩ እስር ቤቶች ውስጥ የነበሩ  የኦብነግ አባሎች ናቸው የተባሉትን ፈትቶ የለቀቃቸው ቢሆንም አሁን ደግሞ መልሶ ከየቦታው እየለቀመ ወደ እስር ቤት እያጎራቸው እንደሚገኝም ከጅጅጋ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በክልሉ ሰላም ሰፍኖዋል ልማትም እየተፋጠነ ነው እያለ የወያኔ ቡድን ቢያናፍስም እውነታው ግን ከአራት ክፍለ ጦር በላይ ሰፍሮ የሚገኝበት እና የክልሉ ነዋሪም በነፃነት እንደ ልቡ የማይንቀሳቀስ መሆኑን ነዋሪዎቹ በምሬት እየገለፁ ናቸው፡፡

በሌላ ዜና  አዲሱ የታክሲ ስምሪት እና ምደባ አያዋጣንም በማለት ባለፈው ሳምንት የተጀመረው የታክሲ ሹፌሮች የስራ ማቆም አድማ ተባብሶ ቀጥሎ መሰንበቱ ታወቀ፡፡የህዝብ ብዛትንና የመኪና አቅርቦትን ያላገናዘበ በይድረስ ይድረስ ብቻ የተዘረጋው የታክሲ ስምሪትን የተቃወሙት ሹፌሮች የስራ ማቆም አድማ በመምታታቸው አዲስ አበባን ጭር አድርገው መሰንበታቸውም ታውቆዋል፡፡

የታክሲ ባለንብረቶች ፣ ሹፌሮችና  ረዳቶች ያቀረቡት ጥያቄ ምላሽ በማጣቱ በተለይ ሰኞ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም በአዲስ አበባ ታክሲዎች የተጀመረውን የስራ ማቆም አድማ በማጠናከራቸው ከተማዋ ጭር ከማለትዋም በተጨማሪ ህዝቡ በትራንስፖርት እጥረት ተቸግሮ እንደነበር ታይቶዋል፡፡

ሰሞኑን በተፈጠረው የታክሲ እጥረት የተነሳ ሰራተኞች ወደ ስራ ገበታቸው ሳይገቡ እየቀሩ በቤታቸው ለመቀመጥ እንደተገደዱ የታወቀ ሲሆን ወያኔ በንግግር እና በመወያየት የማያምን ህዝብን በጠመንጃ ጨፍልቆ እኔ ያልኩትን ብቻ ተቀበሉ የሚል የእውር ድንብር የሚጉዋዝ ቡድን በመሆኑ አሁንም በእኛ ላይ እያደረገ ያለው ይሄንኑ ነው ሲሉ የታክሲ ሹፌሮች በምሬት ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

በተለይ ሰኞ እለት የተደረገውን የታክሲ ስራ ማቆም አድማን ተከትሎ ፖሊሶችና የታክሲ አሽከርካሪዎች ግጭት ፈጥረው በቡጢ ሲቡዋቀሱ የተስተዋለ ሲሆን ህዝቡም በቁጣ በመነሳሳት በፖሊሶች ላይ መጠነኛ አደጋ ሲያደርሱ መታየታቸውንም ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን አስረድቶዋል፡፡

በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ሹፌሮችና ፖሊሶች ግጭት ፈጥረው ፖሊሶች በመሳሪያና በጀርመን ሰራሽ ዱላ .......ሹፌሮችና ረዳቶች ሆነው ደግሞ በድንጋይ ሲፋለሙ የነበረ ሲሆን በተለይ ብርጭቆ ፋብሪካ ተብሎ በሚጠራው ሰፈር ውስጥ በሚገኘው የኮንዶሚኒየም ግቢ ውስጥ ከፍተኛ ድብድብ ተከስቶ ብዙ ፖሊሶች ተፈንክተው የተባረሩ መሆኑን ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ገልፆዋል፡፡

በታክሲዎች የተጀመረው የስራ ማቆም አድማ ወደ ሌሎች ይዛመታል የሚል ፍርሀት የገባው የወያኔ ቡድን በደህንነት ሰራተኞች እና በፖሊስ በኩል ውስጥ ውስጡን የአድማው ቀስቃሽ ናችሁ በሚል ሹፌሮችን ከየቤታቸው እየለቀሙ ኮልፌ በሚገኘው የተወርዋሪ ፖሊስ ካምፕ ውስጥ በማስገባት ይህ ቀረሽ የማይባል የዱላ ድብደባ የፈጸሙባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ለአራት ቀናት ጠዋት ጠዋት የቀዘቀዘ ውሀ በተሞላ በርሜል ውስጥ እራቁታቸውን ለአንድ ሰዓት ያህል እንዲቆዩ መደረጉንም ድርጊቱ ከተፈፀመባቸው ሹፌሮች የደረሰን ዘገባም ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡

ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ዕለት ድረስ ከየቦታው ሹፉሮችን የመልቀሙና የማሰሩ ስራ ተጠናክሮ የቀጠለ ከመሆኑም በላይ ረዳቶቻቸውን ጭምር እያፈሱ ወደ እስር ቤት እያጎሩዋቸው መሆኑም ታውቆዋል፡፡

በተፈጠረው የታክሲዎች የስራ ማቆም አድማ የተደናገጡት የአዲስ አበባ ከተማ የፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖች ለሁለት ቀናት አስቸኩዋይ ስብሰባ አድርገው በሹፌሮቹ ላይ የሚወሰደውን የግፍ እርምጃ አጽድቀውና ተስማምተው በኮልፌ ማሰልጠኛ ካምፕ ውስጥ እንዲታሰሩና ስፖርታዊ የተባለ ድብደባ እንዲፈጸምባቸው ጭምር መስማማታቸውን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

ምንም እንኩዋን በታክሲ ሹፌሮች ላይ የእስራት እና የድብደባ ተግባር እየተፈጸመ ቢሆንም ብዙ ሹፌሮች ያለ ፍርሀት በያዙት አቁዋም በመቀጠላቸው ስራቸውን በማቆማቸው ታክሲዎች በየጋራዡና በየቦታው ቆመው ለመዋል መገደዳቸውን ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋቢያችን ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በመጨረሻም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት መሀከል የተጀመረው ሽኩቻ ተቀጣጥሎ መቀጠሉ ከቤተ ክህነት አከባቢ የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

በዓመት ሁለት ግዜ የሚሰበሰበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሲኖዶስ የዘንድሮው የመጀመሪያ ስብሰባ ጥቅምት ላይ ተደርጎ የአባ ጳውሎስ ምስሎች ከየአደባባዩና ከየቤተክርስቲያኑ እንዲወርድ ሐውልታቸውም እንዲፈርስ ብሎ ወስኖ የነበረ ቢሆንም ሲኖዶሱ ያሳለፈው ውሳኔ ሳይፈጸም በመቅረቱ በሰሞኑ በተደረገው ሁለተኛው ጠቅላላ ስብሰባ የመጀመሪያ አጀንዳ የሆነው ይሄው ጉዳይ እንደነበረ የገለጹት የቤተክህነት ምንጮች በዚህ ላይ ሁለት ቀናት ሰጨቃጨቁ እንደቆዩና ሐውልቱም እንዲፈርስ በድጋሚ መወሰኑን በተጨማሪ ገልጸዋል፡፡

ሌላው የወቅቱ አጀንዳ የነበረው አዳዲስ ጳጳሳት መሾምን የተመለከተ ቢሆንም አባ ጳውሎስ ለጽጽስና የማይበቁ መስፈርቱን የማያሙሉትን የራሳቸውን ስጋ ዘመዶች ሰብስበው ያቀረቡ ቢሆንም ሲኖዶሱ አሁን ያለነው ጳጳሳት ለሀገሪቱ በቂ ከመሆኑም በላይ ያለነውም ስራ ለመስራት ያልተመቻቸበት በመሆኑ አሁን ጳጳሳት መሾሙ አስፈላጊ አይደለም ያም ቢሆን በእጩነት የቀረቡት በሙሉ መስፈርቱን

አያሙዋሉም በማለት በሙሉ ድምፅ የአባ ጳውሎስን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

አንዳንድ ጳጳሳት እንዳሉት ከሆነ በተለይ በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክህነት ውስጥ እየተደረገ ያለው በዘመድ ተጠላልፎ መስራት እና በቡድንተኝነት ላይ ተመስርቶ በእውነት የሚሰሩትን የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን ማጥቃት ከወንጀሎች በላይ ወንጀል ከመሆኑም በላይ እኛ የእምነት አባቶች ድርጊቱን እያየን እና እየሰማን ዝም ማለታችን የወንጀሉ ፈጻሚዎች ተባባሪ ስለሚያስመስለን ከዛሬ ጀምሮ ሁላችንም በየፊናችን ልንታገለው ግድ ይለናል ሲሉ እንደነበረም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በአሁኑ ግዜ በስደት ላይ ከሚገኘው ሲኖዶስ ጋር የተጀመረው እርቅ በስፋት ቀጥሎ እልባት ላይ መድረስ አለበት ያለው የሲኖዶሱ ስብሰባ እርቁ ወርዶ ውጭ ሀገር ያሉት አባቶች ቢመጡ ቁጥራችን እጅግ የበዛ ስለሚሆን አሁን የቀረቡት እጩዎች ለሌላ ግዜ ይተላለፍ ሲል ሲኖዶሱ በመወሰኑ አባ ጳውሎስ ከፍተኛ ቅሬታ እንዳደረባቸውም ምንጮቹ አስረድተዋል::

በቅርቡ ከሞቱት አቡነ መልከ ፀዲቅ ጋር 52 ጳጳሳት የሚገኙበት ሲኖዶስ በሰሞኑ ጠቅላላ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ብዙዎቹ ያልተገኙ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

ሰሞኑን አባ ጳውሎስ ሊያሾሙዋቸው የነበሩት ጳጳሳት ቁጥር 20 እንደነበርና እነሱም የቅርብ ዘመዶቻቸው አልፎም የትውልድ ሀገር ቀረቤታ ያላቸው ብቻ ተመርጠው እንደነበር ያጋለጡት ምንጮቹ ከቤተክህነት ጥበቃ ጀምሮ ያሉት ሰራተኞች የአባ ጳውሎስ የትውልድ ሀገር ሰዎች መሆናቸውንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በዚሁ የሲኖዶሱ ስብሰባ ላይ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ ሲያጨቃጭቅ የዋለው ጉዳይ ከሲኖዶሱ ስልጣን ይልቅ የአባ ጳውሎስ ስልጣን ከግዜ ወደ ግዜ እየገነነ እና እየተስፋፋ አምባገነናዊ አስተዳደር በቤተክህነት ውስጥ መንሰራፋቱን በተመከለተ ሲሆን ይህንንም ከሶስት ጳጳሳት በስተቀር የተቀሩት በሙሉ በአባ ጳውሎስ ላይ ተቃውሞና ትችት ሲያቀርቡባቸው እንደነበረም ምንጮቹ አብራርተዋል::

ከረቡዕ ጀምሮ እስከ አርብ ምሽት ድረስ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ዝግ ስብሰባ ተደርጎ ሀውልቱ እንዲፈርስ...... አባ ጳውሎስ ከሲኖዶሱ የሚሰጣቸውን ስልጣን ብቻ እንዲጠቀሙ......በሚሉትና በሌሎችም ላይ ውሳኔ አሳልፎ መጠናቀቁን ምንጮቹ አስረድተዋል::